# የኢዴፓ መተዳደሪያ ደንብ

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

ኢዴፓ ኢትዮጵያ የሕዝባዊ መንግሥት ባለቤት ሆና ሠላም፣ ዴሞክራሲ፣ እኩልነትና አንድነት የሰፈነባት፣ ርሃብና ድህነት ተወግደው የበለፀገች አገር እንድትሆን በሠላማዊ መንገድ ለመታገል በብሔራዊ ደረጃ የተቋቋመ ፓርቲ ነው።

ፓርቲው በቅድሚያ ሕዝቡን በማንቃትና፣ ነፃና ፍትሃዊ የምርጫ ውድድርን መሣሪያው በማድረግ ከሕዝብ የሚሰጥ የፖለቲካ ሥልጣንን ለመያዝ ወይም ለመጋራት በመላው የአገሪቱ ክፍል ድርጅታዊ መዋቅሩን ዘርግቶ ይታገላል።

የዘር፣ የቀለም፣ የኃይማኖትና የቋንቋ ልዩነት ሳያደርግ ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ በአባልነት በመቀበል "ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለኢትዮጵያ" በሚል መሠረታዊ መርህ ለእኩልነትና ለአንድነት በጽኑ ይታገላል። ፓርቲው ከማዕከል እስከ መሠረታዊ ድርጅት በሚዘረጋው መዋቅሩ የታቀፉ አባሎቹ በመመሪያነት እንዲጠቀሙበት ይህንን የመተዳደሪያ ደንብ አውጥቷል። መተዳደሪያ ደንቡ በፓርቲው ውስጥ አባሎች መብትና ግዴታቸውን አውቀው የሚሳተፉበትን ሁኔታ ያስገነዝባል። በተጨማሪም በአመራር አካሎች፣ በበታች አካሎችና በአባሎች መካከል ዴሞክራሲያዊ የሆነ አሠራር እንዲኖር ያደርጋል።

ደንቡ የፓርቲውን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የግልና የጋራ ኃላፊነት በተጣጣመ መልኩ በስራ ላይ የሚውሉበትን መርሆዎች ያካተተ ነው። መተዳደሪያ ደንቡ የአባሎችን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ የውክልና አሠራርን እንደ ዋነኛ የአሠራር ሥልት ይጠቀማል።

በፓርቲው ውስጥ የአባሎች የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት እንዲኖር፣ የሥራ ተነሳሽነትና የዓላማ ጽናት እንዲያድግ ያበረታታል። በአጠቃላይ የፓርቲው እንቅስቃሴ ቀልጣፋ፣ አስተማማኝና አመርቂ እንዲሆን እውቀትን፣ ገንዘብንና ጊዜን ባቀናጀ መልኩ የአባሎች ተሳትፎ መጠናከርን ከመርሆዎቹ ውስጥ በዋነኛነት ይጠቅሳል።

## አንቀጽ 1፣ መቋቋም

በአገር አቀፍ ፓርቲነት ተመዝግቦ ይንቀሳቀስ የነበረው ኢዴአፓ-መድህን ፓርቲ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 36 መሠረት መተዳደሪያ ደንቡንና ፕሮግራሙን በማሻሻል "ኢዴፓ" በሚል ስያሜ ተተክቷል።

## አንቀጽ 2፣ አጭር ርዕስ

ይህ መተዳደሪያ ደንብ የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) መተዳደሪያ ደንብ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## አንቀጽ 3፣ የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት

የፓርቲው ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ሲሆን ካስፈለገ ወደ ሌላ ከተማ ለማዛወር ይቻላል። እንደ አስፈላጊነቱ በሌሎች ቦታዎች ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይኖሩታል።

## አንቀጽ 4. አባልነት

### 4.1 እጩ አባል

4.1.1 ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣ የፓርቲውን ዓላማዎችና እምነቶች ተቀብሎ የአባልነት ቅጽ የሞላና ለተግባራዊነታቸው ማንኛውንም አስተዋጽኦ ለማድረግና በቁርጠኝነት ለመታገል ዝግጁ የሆነ፣

4.1.2 የኢትዮጵያን ሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና የበላይነት የሚቀበልና በአገሪቱ ሃቀኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን በጽኑ ለመታገል የመረጠ፣

4.1.3 የፓርቲውን ወርሃዊ ክፍያ ለመክፈልና ሌሎች ግዴታዎችንም ለመፈፀም ፈቃደኛና ዝግጁ የሆነ፣

4.1.4 የፓርቲውን አመራር ውሳኔዎች ተግባራዊ ለማድረግ ፈቃደኛ የሆነና ግዴታው መሆኑን የሚቀበል፣

4.1.5 እድሜው 18 ዓመት የሞላና የሌላ የፖለቲካ ድርጅት አባል ያልሆነ፣

4.1.6 በፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ እና/ወይም በወረዳ ምክር ቤት በኩል አባል እንዲሆን ጥያቄ ቀርቦለት ጥያቄውን የተቀበለ፣

አባል ለመሆን ሲጠይቅ በእጩ አባልነት ይመዘገባል::

### 4.2 ሙሉ አባል፣

የፓርቲው እጩ አባል ሆኖ ከተመዘገበ እስከ 180ኛው ቀን ድረስ የዲሲፕሊን ግድፈት ያልተገኘበትና የአባልነት ግዴታውን በአግባቡ የተወጣ፣ የፓርቲው ሙሉ አባል ይሆናል፡፡

### 4.3 ተባባሪ አባል፣

በፓርቲው ውስጥ ሙሉ ተሳትፎ ለማድረግ የግል ሁኔታቸው የማይፈቅድላቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተባባሪ አባል ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ለፓርቲ ኃላፊነት ለመመረጥ ካለመቻል በስተቀር ሌሎች የአባልነት መብቶች ሁሉ ይኖራቸዋል፡፡

## አንቀጽ 5፣ የአባልነት መብት፣

### 5.1 የእጩ አባል መብት፣

እጩ አባል በመሠረታዊ ድርጅት ውስጥ ተሳታፊ የመሆንና የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ አስፈላጊ መሆኑን ካመነበት ለመሠረታዊ ድርጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት ሊመረጥ ይችላል፡፡

### 5.2 ሙሉ አባል፣

**ሙሉ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡**

5.2.1 በፓርቲው ስብሰባዎች ሃሳብ የማቅረብና ድምጽ የመስጠት፣

5.2.2 የመምረጥና የመመረጥ፣

5.2.3 የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መከበሩንና ከፕሮግራሙ ያልወጣ ተግባር መፈፀሙን የመከታተል፣

5.2.4 ድርጅታዊ መዋቅርን ጠብቆ ማብራሪያና መረጃ የመጠየቅና ገንቢ ሂስ የማቅረብ፣

5.2.5 በራስ ተነሳሽነት አዳዲስና ጠቃሚ ሃሳቦችን የማፍለቅ፣ ለፓርቲ አመራር የማስተላለፍ፣ በፓርቲ እንቅስቃሴዎችና ተግባሮች የመሳተፍ፣

5.2.6 አንድ የፓርቲ አባል በራሱ ፍላጐት አባልነቱን የማቋረጥ፣ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 6፣ የአባልነት ግዴታ፣

**ማንኛውም የፓርቲው አባል፤**

6.1 የፓርቲውን ዓላማና ፕሮግራም ተግባራዊ የማድረግ፣

6.2 በተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችና ፓርቲው በሚጠራቸው የተለያዩ ስብሰባዎች በመሳተፍ ድርጅታዊ ግዴታን የመወጣት፣

6.3 የፓርቲውን ፕሮግራምና ዓላማ አንድነትና ህብረት ከሚጐዱ ማናቸውም እንቅስቃሴዎችና የሥነ-ምግባር ጉድለቶች የመቆጠብ፣

6.4 ለፓርቲው ታማኝ የመሆንና ሚስጥር የመጠበቅ፣

6.5 የአባልነት መዋጮን በወቅቱ መክፈልና በፓርቲው የገቢ ማሰባሰቢያ (Fund Raising) ተግባራት የመሳተፍ፣

6.6 የፓርቲውን ዓላማዎችና እምነቶች ለሕዝብ የማስተዋወቅና የማሠራጨት፣

6.7 ሌሎች ከፓርቲው አመራር አካላት የሚሰጡ ተግባራትን የማከናወን፣

6.8 ፓርቲውን ወክሎ ለመንግስት ምክር ቤቶች አባልነት በሕዝብ ሲመረጥ በፓርቲው ደንብና ፕሮግራም መሰረት አስፈላጊውን የመፈጸም፣ ግዴታ አለበት፡፡

# ክፍል ሁለት

# የአመራር አካሎች፣ አመሰራረት፣ ሥልጣንና ተግባር፣

## አንቀጽ 7፣ የአመራር አካሎች፣

ኢዴፓ የሚከተሉት የአመራር አካሎች ይኖሩታል፡፡

7.1 ጠቅላላ ጉባዔ፣

7.2 ምክር ቤት፣

7.3 የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ፣

7.4 ማዕከላዊ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣

7.5 የክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴ፣

7.6 ወረዳ ምክር ቤት፣

7.7 ወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣

7.8 መሠረታዊ ድርጅቶች፣

7.9 ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች፡፡

## አንቀጽ 8፣ የጠቅላላ ጉባዔ አመሠራረት፣ ሥልጣንና ተግባር፣

### 8.1 ስለ ጠቅላላ ጉባዔው፣

ጠቅላላ ጉባዔው የኢዴፓ ከፍተኛ የሥልጣን አካል ነው፡፡

### 8.2 የጠቅላላ ጉባዔው አመሰራረት፣

የጠቅላላ ጉባዔው አባሎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

8.2.1 የፓርቲው ምክር ቤትና የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባላት፣

8.2.2 የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሰብሳቢዎች፣

8.2.3 በፓርቲው ምክር ቤት ከሚቋቋሙ የክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴዎች የሚወከሉ ሦስት፣ ሦስት ተወካዮች፣

8.2.4 እንደ አስፈላጊነቱ በውጭ አገር ከሚቋቋሙ የድጋፍ ኮሚቴ አባሎች መካከል በማዕከላዊ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሚመረጡ ከአምስት ያልበለጡ ተወካዮች፣

### 8.3 የጠቅላላ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር፣

ጠቅላላ ጉባዔው የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል::

8.3.1 የፓርቲውን ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ያወጣል፣ በዓቢይ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣

8.3.2 ሶስት አባላት ያሉት አስመራጭ ኮሚቴ በመሰየም፣ የማዕከላዊ ምክር ቤት አባሎችን ይመርጣል፣

8.3.3 የማዕከላዊ ምክር ቤቱን ሥራ ይገመግማል፣

8.3.4 የኦዲትና ኢንስፔክሽን፣ ኮሚቴ አባሎችን ይመርጣል፣ ይሸራል፣

8.3.5 ከማዕከላዊ ምክር ቤትና ከኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ የሚቀርቡለትን የሥራ ክንውን ሪፖርቶች እየመረመረ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፣

8.3.6 ፓርቲው ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር የሚመሰርታቸውን ከህብረት እስከ ውህደት የሚደርሱ የትግል ግንኙነቶችንና ስምምነቶችን ይገመግማል፣ ያፀድቃል፣

8.3.7 ፓርቲውን በሚመለከቱ በማናቸውም ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል፣

8.3.8 የፓርቲውን ፕሮግራምና ደንብ ያፀድቃል፣ ይለውጣል፣ ያሻሽላል፣

8.3.9 የፓርቲውን ስም፣ ዓርማና መዝሙር ያፀድቃል፣

8.3.10 የምክር ቤቱ አባላት ቢጎደሉ የማሟላት ኃላፊነቱን ለምክር ቤቱ ውክልና ይሰጣል፣

8.3.11 የጠቅላላ ጉባዔው የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል። ሆኖም ጉባዔውን በመደበኛ ወቅቱ መጥራት የማይቻልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ምክር ቤቱ እስከ አንድ ዓመት ሊያራዝመው ይችላል።

# አንቀጽ 9፣ የፓርቲው ምክር ቤት አመሰራረት፣ ሥልጣንና ተግባር፣

## 9.1 ስለ ምክር ቤቱ፣

ምክር ቤቱ ከጠቅላላ ጉባዔው ቀጥሎ የፓርቲው ከፍተኛው የሥልጣን አካል ነው::

## 9.2 የፓርቲው ምክር ቤት አመሰራረት፣

የምክር ቤቱ አባሎች የሚከተሉት ናቸው።

9.2.1 ከጠቅላላ ጉባዔው አባሎች መካከል የሚመረጡ 23 አባላት፣ ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን የሴቶች ተሳትፎ እንዲበረታታ ይደረጋል።

9.2.2 ከመሰል የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በሚፈጠር ውህደት ላይ ተመስርቶ የአባሎች ብዛት ከላይ በንዑስ ቁጥር 9.2.1 ከተመለከተው ቁጥር ሊበልጥ ይችላል።

9.2.3 ምክር ቤቱ ከክፍለ-ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴዎች ተወካዮችን እንዳስፈላጊነቱ በመጋበዝ ድምጽ አልባ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሊያደርግ ይችላል።

9.2.4 ከምክር ቤቱ አባላት መሀል በተለያየ ምክንያት መጉደል ቢፈጠር እስከ ጠቅላላ ጉባዔው ድረስ ተክቶ እንዲያሰራና ለጉባዔው ሪፖርት እንዲያደርግ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ውክልና ተሰጥቷል።

## 9.3 ስለ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ፣

ምክር ቤቱ የራሱን ሰብሳቢ ይመርጣል፣ ሰብሳቢውም የሚከተሉትን ተግባሮች ያከናውናል::

9.3.1 የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣

9.3.2 ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው መደበኛ የስብሰባ ጊዜን ጠብቆ ስብሰባ እንዲጠራ ያሳስባል::

## 9.4 የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር፣

ምክር ቤቱ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል::

9.4.1 በጠቅላላ ጉባዔው የፀደቁ ፖሊሲዎችንና መመሪያዎችን እንዲሁም ሌሎች ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል።

9.4.2 የጠቅላላ ጉባዔውን መደበኛ፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣

9.4.3 በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባዎች መካከል ባለው ጊዜ በሀገሪቱና በፓርቲው ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔዎችን ያሳልፋል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱ አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባዔ ጥሪ ያደርጋል።

9.4.4 ስለ ፓርቲው የሥራ ክንውን ለጠቅላላ ጉባዔው ሪፖርት ያቀርባል፣

9.4.5 ለጠቅላላ ጉባዔ አባልነት የሚያበቃ መዋቅር ውስጥ ያልተካተቱ ሃያ አባሎችን ለጠቅላላ ጉባዔ አባልነት ይመርጣል፣

9.4.6 የፓርቲውን ዓላማዎች ለማስፈፀም የሚያስችሉ የክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴዎችንና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን ያቋቁማል፣ ኃላፊነታቸውን ይወስናል፣ ስራቸውንም ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል።

9.4.7 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ሥራ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣

9.4.8 በማዕከላዊ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሚቀርብለትን የፓርቲውን የሥራና የበጀት ዕቅድ መርምሮ ያፀድቃል፣

9.4.9 የጸደቁ የሥራ እቅዶች መፈፀማቸውንና በጀቱም በአግባቡ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

9.4.10 ሙሉ ጊዜያቸውን በፓርቲው ሥራ ላይ ማዋል ስላለባቸው አባሎችና ሌሎች ሠራተኞችን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፣ መመሪያውም በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

9.4.11 በዲስፕሊን ጉዳዮች ላይ የመጨረሻውን ውሳኔ ይሰጣል። ሆኖም የማዕከላዊ ምክር ቤት አባልን በተመለከተ የዲሲፕሊን ውሣኔው የሚፀናው በምክር ቤቱ ሁለት ሦስተኛ ወይም ከዚያ በበለጡ አባሎች ሲደገፍ ነው።

9.4.12 ይህንን መተዳደሪያ ደንብ መሠረት አድርጎ፣ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች አወሳሰድን፣ የገንዘብና የንብረት አስተዳደርን እና ሌሎች ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያዎችን ያወጣል፣ ተግባራዊነታቸውንም ይከታተላል፣

9.4.13 ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሊኖር ስለሚገባ ግናኙነትም የትግል ግንኙነት ላይ መመሪያና ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔውንም ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያፀድቃል፣

9.4.14 ከመሰል የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በሚፈጠሩ የውህደት ስምምነቶች ላይ ተመስርቶ የምክር ቤቱን አባሎች ብዛት በጊዜያዊነት እስከ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ ድረስ እንደ አስፈላጊነቱ ከፍ ወይም ዝቅ ሊያደርገው ይችላል።

9.4.15 ፓርቲውን ወክለው በወረዳና ከዚያ በላይ ባሉ ደረጃዎች በምርጫ የሚሳተፉ አባሎችን ይመርጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል።

9.4.16 ከጠቅላላ ጉባዔው አባሎች መካከል ለፓርቲው ምክር ቤት አባልነት ምርጫ የሚቀርቡ ከ23 ያላነሱና ከ30 ያልበለጡ እጩዎችን መልምሎ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል። ጠቅላላ ጉባዔው ከፈለገ ምክር ቤቱ ካቀረባቸው እጩዎች ብዛት በተጨማሪ እስከ 25% የሚደርሱ ዕጩዎችን ማቅረብ ይችላል።

9.4.17 ከመካከሉ የፓርቲውን ሊቀ መንበር፣ ም/ሊቀ መንበር፣ ዋና ጸሐፊ እና ሌሎች የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል፣ ይሽራል፣

9.4.18 የፓርቲውን ዓርማና መዝሙር ያዘጋጃል፣ ያሻሽላል፣ ለጠቅላላ ጉባዔውም አቅርቦ ያፀድቃል፣

9.4.19 ምክር ቤቱ ከሥልጣኑ ከፊሉን ለማዕከላዊ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ፣ ለወረዳ ምክር ቤቶችና ለክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

9.4.20 ከጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል።

# አንቀጽ 10፣ የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አመሠራረት፣ ሥልጣንና ኃላፊት

ሦስት ብቃት ያላቸው አባሎች የሚመሩት የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔ ይመረጣል። ተጠሪነቱም ለጠቅላላ ጉባዔው ሆኖ በምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ ላይ በመገኘት ሪፖርት ያቀርባል። የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶችም ይኖሩታል።

10.1 የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

10.2 የፖሊሲ ነክ ስህተቶች ወይም የአሠራር ጉድለቶች ሲፈጸሙ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን በወቅቱ እንዲታረሙ ያደርጋል፣

10.3 የማይታረሙ ወይንም ከአቅም በላይ የሆኑ ስህተቶች ሲፈጠሩ ¼ኛ የጠቅላላ ጉባዔ አባሎችን የድጋፍ ፊርማ በማሰባሰብ የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ እንዲጠራና ጉድለቶቹ እንዲታረሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣

10.4 ለጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ያቀርባል፣ ለተከሰቱ ችግሮችም የመፍትሔ ሃሳብ ይጠቁማል፣

10.5 በጠቅላላ ጉባዔ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

10.6 የኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ አባሎች የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል::

## አንቀጽ 11፣ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አመሠራረት፣

የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከምክር ቤቱ አባሎች መካከል በተመረጡ ሰባት አባሎች ይቋቋማል:: እነሱም፡-

11.1 የፓርቲው ፕሬዝዳንት፣

11.2 ምክትል ፕሬዝዳንት፣

11.3 ዋና ፀሐፊ፣

11.4 የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

11.5 የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣

11.6 የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፣

11.7 የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ፣ ናቸው።

## አንቀጽ 12፣ የፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣

የማዕከላዊ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል።

12.1 ከፕሬዝዳንቱ፣ ከምክትል ፕሬዝዳንቱና ከዋና ፀሐፊው ቀጥሎ ያሉ የየዘርፍ የሥራ ኃላፊነቶችን ድልድል ያከናውናል።

12.2 የምክር ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ያውላል፣

12.3 የፓርቲውን ዓላማዎች ለማስፈጸም የሚያስችሉ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል። ከሚቋቋሙት ኮሚቴዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፣

12.3.1 የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣

12.3.2 የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ፣

12.3.3 የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣

12.3.4 የፋይናንስ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣

12.4 የምክር ቤቱን መደበኛ፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል፣

12.5 የፓርቲውን የሥራና የበጀት እቅድ ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል፣

12.6 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

12.7 በየአራት ወሩ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

12.8 በፓርቲው ስም ስምምነቶችና ውሎችን ይፈፅማል፣

12.9 ፓርቲው አቋም በወሰደባቸው ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ይሰጣል፣

12.10 የሥራ ኃላፊዎችና ኮሚቴዎች ተግባራቸውን በሚገባ መወጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ይቆጣጠራል፣ ይከታተላል፣

12.11 ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ሊኖር የሚገባው የትግል ግንኙነትን በተመለከተ የምክር ቤቱን ውሳኔና መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፣

12.12 ከሥልጣኑ ከፊሉን ለሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎችና ሌሎች የሥልጣን አካላት በውክልና ሊሰጥ ይችላል።

12.13 ለፓርቲው ዓላማና ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉትን የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ያሰባስባል፣

12.14 አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥናትና ምርምር የሚያካሂድ (Think Thank) ቡድን ያቋቁማል፣ ስራና ኃላፊነቱን ይወስናል፣

12.15 ከምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

# አንቀጽ 13፣ የክፍለ-ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴ አመሠራረት፣

13.1 የክፍለ-ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴ በፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አማካኝነት በሚመረጡና ምክር ቤቱ በሚያፀድቃቸው አምስት አባሎች ይቋቋማል። እነርሱም፡-

13.1.1 ሰብሳቢ፣

13.1.2 ምክትል ሰብሳቢ፣

13.1.3 ፀሐፊ፣

13.1.4 የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

13.1.5 የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ ናቸው።

13.2 የክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል።

# አንቀጽ 14፣ የክፍለ-ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር፣

የክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል::

14.1 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ያውላል፣

14.2 በክፍለ-ሀገሩ ውስጥ የፓርቲውን ዓላማዎች ለማስፈፀም የሚያስችሉ የተለያዩ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል ኃላፊነታቸውንም ይወስናል፣

14.3 የየዘርፍ ምክትል ኃላፊዎችን መርጦ በእጩነት በማቅረብ በፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ያጸድቃል፣

14.4 የክፍለ-ሀገሩን የሥራና የበጀት እቅድ ለፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አቅርቦ ያፀድቃል፣

14.5 የአስተባባሪ ኮሚቴውና የወረዳ ጽህፈት ቤቶች ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

14.6 በአጠቃላይ ስለ ክፍለ-ሀገሩ በተለይም ስለ አስተባባሪ ኮሚቴው የሥራ እንቅስቃሴ ለፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሪፖርት ያቀርባል፣

14.7 የሥራ ኃላፊዎችና ኮሚቴዎች ተግባራቸውን በሚገባ መወጣታቸውን ይቆጣጠራል፣

14.8 እንደ አስፈላጊነቱ ከሥልጣኑ ከፊሉን ላቋቋማቸው ኮሚቴዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣

14.9 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

# አንቀጽ 15፣ የወረዳ ምክር ቤት አመሠራረት፣ ሥልጣንና ተግባር፣

## 15.1 የወረዳ ምክር ቤት አመሠራረት፣

የወረዳ ምክር ቤት አባሎች የሚከተሉት ናቸው::

15.1.1 ቁጥራቸው በፓርቲው ምክር ቤት መመሪያ በሚወሰን ከየመሠረታዊ ድርጅቶች የተውጣጡ አባሎች፣

15.1.2 የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች፣

15.1.3 እንደ ፓርቲው ተጨባጭ ሁኔታ በወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሚመረጡ ሴቶች፣

15.1.4 በወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከሚቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚሰየሙ አንድ፣ አንድ ተወካዮች፣

### 15.2 የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ሁለት አመት ይሆናል፣

### 15.3 የወረዳ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባሮች፣

የወረዳ ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለክፍለ-ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴ ሆኖ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፣

15.3.1 በፓርቲው ምክር ቤት የተላለፉ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

15.3.2 በምክር ቤቱ የጸደቁና በወረዳው የሥልጣን ክልል ውስጥ ያሉ የሥራ እቅዶች መፈፀማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

15.3.3 ለቀበሌ መስተዳድር ምክር ቤቶች አባልነት የሚወዳደሩ ዕጩዎችን ይመርጣል፣ በበላይ አካሎች አስጸድቆ በእጩነት ያቀርባል፣

15.3.4 የወረዳውን በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

15.3.5 ከምክር ቤቱ አባሎች ውስጥ የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሎችን ይመርጣል፣ ይሽራል፣

15.3.6 የምክር ቤቱን መመሪያ መሠረት በማድረግ መሠረታዊ ድርጅቶችን ያቋቁማል፣

15.3.7 የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴን ሥራ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣

15.3.8 በዲሲፕሊን ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣

15.3.9 ከበላይ አመራር አካሎች የሚሰጡትን ሌሎች ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 16፣ የወረዳ ስራ አስኪያጅ ኮሚቴ አመሠራረት፣

16.1 የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ከወረዳው ምክር ቤት አባሎች መካከል በተመረጡ አምስት አባሎች ይቋቋማል፡፡ እነሱም፡-

16.1.1 ሰብሳቢ፣

16.1.2 ም/ሰብሳቢ፣

16.1.3 ፀሐፊ፣

16.1.4 የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

16.1.5 የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣

16.2 የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሥራ ዘመን የወረዳ ምክር ቤት የሥራ ዘመን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 17፣ የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ሥልጣንና ተግባር፣

የወረዳ ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለወረዳ ምክር ቤት ሆኖ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

17.1 የወረዳ ምክር ቤቱን ውሳኔዎችና መመሪያዎች በሥራ ላይ ያውላል፣

17.2 ልዩ ልዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ ተግባራቸውን በሚገባ ማከናወናቸውን ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

17.3 እንደ ፓርቲው ተጨባጭ ሁኔታ ከአባሎች መካከል ሴቶችን ለወረዳ ምክር ቤት አባልነት ይመርጣል፣

17.4 ለወረዳ ምክር ቤት ስብሰባዎች አጀንዳዎችን ያዘጋጃል፣ በአስቸኳይ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣ ለወረዳ ምክር ቤት አቅርቦም ያፀድቃል፣

17.5 ስለ ሥራው እንቅስቃሴ ለወረዳ ምክር ቤትና በክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴ አማካይነት ለፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ በየሦስት ወሩ ሪፖርት ያቀርባል፣

17.6 ድንገተኛ ሁኔታ ሲፈጠር ልዩና አስቸኳይ የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባዎችን ይጠራል፣

17.7 ከወረዳ ምክር ቤትና ከፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

# አንቀጽ 18፣ መሠረታዊ ድርጅት፣

18.1 መሠረታዊ ድርጅት የፓርቲው ምክር ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በወረዳ ምክር ቤት አማካኝነት ይቋቋማል።

18.2 ከጠቅላላው መሠረታዊ ድርጅት አባሎች የተመረጡ አምስት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባሎች ይኖሩታል፣

18.3 አባሎችን በመመልመል በወረዳ ምክር ቤት እያጸደቀ ያደራጃል፣

18.4 የፓርቲውን ፕሮግራም ያስተዋውቃል፣

18.5 ከአባሎች መዋጮዎችን እየሰበሰበ ለበላይ አካል ያስረክባል፣

18.6 በበላይ አካል የሚሰጠውን ደንብና መመሪያ በተግባር ያውላል፣

18.7 አባሎችን በተመለከተ ልዩ ልዩ መረጃዎችን የሚይዝበት ማህደር ያዘጋጃል፣ በበላይ አካል ሲጠየቅም መረጃዎችን ያስተላልፋል፣

18.8 በወረዳ ምክር ቤት እንዲሰጡ የተፈቀዱ የአባልነት መታወቂያዎችን ለአባሎች ያስተላልፋል፣

18.9 ከወረዳ ምክር ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

# አንቀጽ 19፣ የምርጫ ሥርዓት

## 19.1 የፓርቲው ምክር ቤት አመራረጥ፣

19.1.1 በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰየመው አስመራጭ ኮሚቴ በፓርቲው ምክር ቤት የቀረቡትን የእጩዎች ዝርዝር ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል።

19.1.2 ስለ እጩ አባላቱ ገለፃ በመስጠት ድጋፍና ተቃውሞ ይጠይቃል።

19.1.3 ከፍተኛ ተቃውሞ የቀረበበት እጩ በፍቃዱ እራሱን ካላገለለ ድምጽ እንዲሰጥበት ያደርጋል።

19.1.4 የሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ ተከናውኖ ከፍተኛ የድምጽ ብልጫ ያገኙት የመጀመሪያዎቹ 23 ተመራጮች የፓርቲው ምክር ቤት አባል ይሆናሉ። ሶስት አባላትን በተጠባባቂነት ይያዛሉ፣ ማዕከላዊ ኮሚቴው በተጓደለ ጊዜ እየገመገመ ያሟላል።

## 19.2 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አመራረጥ፣

19.2.1 በጠቅላላ ጉባዔ የሚመረጠው የፓርቲው ምክር ቤት ከመካከሉ ሰባት የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባላትን ይመርጣል።

19.2.2 የስራ አስኪያጅ ኮሚቴው ለፕሬዝዳንትነት፣ ለምክትል ፕሬዝዳንትነትና ለዋና ፀሐፊነት ከመካከሉ አምስት እጩዎችን ለምክር ቤቱ አቅርቦ በየተራ ያስመርጣል።

# አንቀጽ 20፣ ስብሰባና ውሳኔ አሰጣጥ፣

## 20.1 የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ፣

20.1.1 የጉባዔው መደበኛ ስብሰባ በሁለት ዓመት አንድ ጊዜ ይሆናል። ሆኖም ምክር ቤቱ ሲወስን ወይም ከጉባዔው አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የጠቅላላ ጉባዔው ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

20.1.2 የጉባዔው ስብሰባ ምክር ቤቱ በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል።

### 20.2 የፓርቲው ምክር ቤት ስብሰባ፣

20.2.1 የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ በአራት ወር አንድ ጊዜ ይሆናል። ሆኖም የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ሲወስን ወይም ከምክር ቤቱ አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የምክር ቤቱ ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

20.2.2 የምክር ቤቱ ስብሰባ የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል።

### 20.3 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ፣

20.3.1 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜ በመደበኛነት በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ይሆናል። ሆኖም ፕሬዝዳንቱ ሲወስን ወይም ከኮሚቴው አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ ኮሚቴው ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

20.3.2 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባ በመደበኛነት በፓርቲው ጽ/ቤት ይካሄዳል። የስብሰባ ጊዜው በፕሬዝዳንቱና በዋና ጸሐፊው ይወሰናል።

### 20.4 የወረዳ ምክር ቤት ስብሰባ፣

20.4.1 የወረዳ ምክር ቤት መደበኛ ስብሰባ በሦስት ወር አንድ ጊዜ ይሆናል። ሆኖም የወረዳ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴው ሲጠይቅ ወይም ከምክር ቤቱ አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የምክር ቤቱ ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

20.4.2 የወረዳ ምክር ቤቱ ስብሰባ የወረዳው ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በሚወስነው ቦታና ጊዜ ይካሄዳል።

### 20.5 የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ስብሰባ፣

የወረዳ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜ በመደበኛነት በአስራ አምስት ቀን አንድ ጊዜ ይሆናል። ከኮሚቴው አባሎች 1/3ኛዎቹ ሲጠይቁ የኮሚቴው ልዩ ወይም አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።

### 20.6 ውሳኔን እንደገና ስለማየት፣

አንድ ውሳኔ ውሎ አድሮ እንደገና እንዲታይ ከተፈለገ ከአባሎቹ 1/3ኛዎቹ ለፕሬዝዳንቱ (ለሰብሳቢው) በጽሁፍ አቤቱታ ማቅረብ አለባቸው። ከዚህ በኂላ ጉዳዩ እንደገና ይታያል። ቀደም ብሎ የተላለፈው ውሳኔ ለፓርቲው ጉዳት የሚያስከትል ከሆነና ከሚቀጥለው ስብሰባ በፊት ተፈፃሚነት የሚያገኝ ከሆነ ፕሬዝዳንቱ አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራና እንደገና እንዲወሰን ያደርጋል። ሆኖም ይህ አሠራር በአንድ ጉዳይ ላይ ከአንዴ በላይ በተግባር ላይ አይውልም።

## አንቀጽ 21 የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት፣

21.1 ማንኛውም የፓርቲው ስብሰባ ከግማሽ በላይ በሆኑ አባሎች ውክልና ሊካሄድ ይችላል።

21.2 ደንብና ፕሮግራምን ከሚመለከቱ ጉዳዮች በስተቀር በፓርቲው ውስጥ ውሳኔዎች የሚፀድቁት ከግማሽ በላይ በሚሆኑ አባሎች ሲደገፉ ነው።

21.3 በፓርቲው ስብሰባዎች ላይ የውሳኔ ድምጽ በሚሰጥበት ጊዜ እኩል እኩል ድምጽ ከመጣ ሊቀመንበሩ (ሰብሳቢው) ያለበት ወገን ውሳኔ ተቀባይነት ያገኛል።

21.4 አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በተሰብሳቢዎች ውሳኔ መሠረት ሚስጥራዊ የድምጽ አሰጣጥ ሥርዓት ሊካሄድ ይችላል።

# ክፍል ሦስት

# የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አመራር ኃላፊዎች

## አንቀጽ 22፣ ፕሬዝዳንት፣

ፕሬዝዳንቱ በፓርቲው ምክር ቤት ይመረጣል፣ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነትና ሥልጣን ይኖሩታል::

22.1 የፓርቲውን የእለት ተእለት ተግባራት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በበላይነት ይመራል፣

22.2 ፓርቲውን በህጋዊ ሰውነት ይወክላል፣

22.3 የፓርቲው ዓላማዎች፣ ፕሮግራም፣ ደንብ፣ ውሳኔዎችና መመሪያዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣

22.4 በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውሳኔ መሠረት ፓርቲውን በመወከል ልዑካንን ይመራል፣ በተለያዩ ጉባዔዎች ላይ ይገኛል፣ ውል ይዋዋላል፣

22.5 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች ጋር በመመካከር በፓርቲው ስም መግለጫ ይሰጣል፣ ወይም ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች መካከል መግለጫ እንዲሰጡ ውክልና ይሰጣል፣

22.6 በፓርቲው የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት ወጭዎችን ያዛል፣ የፓርቲውን ሂሳብ በፊርማቸው ለማንቀሳቀስ ሥልጣን ከተሰጣቸው ኃላፊዎች ጋር በመሆን የፓርቲውን ሂሳብ በጣምራ ያንቀሳቅሳል፣

22.7 የፓርቲው ልሣን በጥራትና በወቅቱ ተዘጋጅቶ እንዲታተምና እንዲሰራጭ የተለየ ኃላፊነት ይኖረዋል፣

22.8 በምክር ቤቱና በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ውሳኔ መሠረት የሚወጡ ደብዳቤዎችንና ሠነዶችን እንዲሁም ሌሎች አስተዳደር ነክ ደብዳቤዎችን ይፈርማል፣

22.9 ከምክር ቤቱና ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 23፣ ምክትል ፕሬዝዳንት፣

ምክትል ፕሬዝዳንቱ በምክር ቤቱ ይመረጣል፣ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነቶችና ሥልጣን ይኖረዋል::

23.1 በማንኛውም የፓርቲው እንቅስቃሴ ላይ ፕሬዝዳንቱን ይረዳል።

23.2 በተለያዩ አካባቢዎች ለሕዝብ ምክር ቤቶች ለመወዳደር በእጩነት የቀረቡም ሆነ ተወዳድረው የተመረጡ የፓርቲው አባሎችን ጉዳይ በቅርብ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

23.3 በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የተቋቋሙ ቋሚ ኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣

23.4 ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፣

23.5 ከማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፣

## አንቀጽ 24፣ ዋና ፀሐፊ፣

ዋና ፀሐፊው በፓርቲው ምክር ቤት ይመረጣል፣ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነቶችና ሥልጣን ይኖረዋል።

24.1 የፓርቲውን ዋና ጽህፈት ቤትና ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶችን በበላይነት ይመራል፣

24.2 የጽህፈት ቤቱን የደብዳቤ ልውውጦች ያከናውናል፣ የጽህፈት ቤቱ ሰነዶች ሁሉ በሥርዓት መያዛቸውንና መጠበቃቸውን ያረጋግጣል፣

24.3 የጠቅላላ ጉባዔውን፣ የምክር ቤቱንና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውን ቃለ-ጉባዔዎች ይይዛል፣

24.4 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው በሚያወጣው የውስጥ ደንብና መመሪያ መሠረት የፓርቲውን ጊዜያዊና ቋሚ ሠራተኞች ይቆጣጠራል፣ ያሰናብታል፣

24.5 የፓርቲውን ሂሳብ በፊርማቸው ለማንቀሳቀስ ሥልጣን ከተሰጣቸው ኃላፊዎች ጋር በመሆን በጣምራ ያንቀሳቅሳል፣

24.6 የሥራ አስኪይጅ ኮሚቴው በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የጠቅላላ ጉባዔው፣ የምክር ቤቱና የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል፣

24.7 ወደ ፓርቲው ጽህፈት ቤት የሚመጡ እንግዶችን እየተቀበለ ያነጋግራል፣ ተገቢውን መረጃ ይሰጣል፣ ከሚመለታቸው ክፍሎች ጋር ያገናኛል፣

24.8 ስለ ጽህፈት ቤቱ የሥራ አንቅስቃሴ ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ዘገባዎች ያቀርባል።

24.9 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና ከፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 25፣ የድርጅት ጉዳይ ኃላፊ፣

የድርጅት ጉዳይ ኃላፊው ከፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች መካከል የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነቶችና ሥልጣን ይኖረዋል።

25.1 አዳዲስ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ ስልት ይቀይሳል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል።

25.2 አባሎች ለፓርቲው ዓላማና ዲሲፕሊን ተገዥ እንዲሆኑ ክትትል ያደርጋል፣

25.3 የአባሎችን ደህንነትና የሥራ እንቅስቃሴ ለመከታተል የሚያስችሉ መዋቅሮችን ይዘረጋል።

25.4 የፓርቲው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዓላማዎች ወደ አባሎች እንዲሰርፁ ጥረት ያደርጋል።

25.5 ለማደራጀት ሥራው የሚያስፈልጉ የተለያዩ ምክር ቤቶችና ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣

25.6 የድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ኮሚቴዎች በሰብሳቢነት ይመራል፣

25.7 የወረዳ ምክር ቤቶችንና የክፍለ ሀገር አስተባባሪ ኮሚቴዎችን የሥራ እንቅስቅሴ ይከታተላል፣ ያስተባብራል፣

25.8 በፓርቲው ውስጥ የሴቶች ተሳትፎ እንዲጎለብት አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣

25.9 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና ከፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 26፣ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ከፓርቲው ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች መካከል የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነቶችና ሥልጣን ይኖረዋል።

26.1 የፓርቲውን የፕሬስ መግለጫዎች፣ የፕሬስ ኮንፈረንሶች፣ አውደ-ጥናቶችንና ሕዝባዊ ስብሰባዎችን ያዘጋጃል፣ ያስተባብራል፣

26.2 የፓርቲው ልሳን፣ የቅስቀሳ ጽሑፎች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ወዘተ. እንዲዘጋጁና እንዲሰራጩ ያደርጋል፣

26.3 ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳን የሚመለከቱ እንቅስቃሴዎችን ያቅዳል፣ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል።

26.4 ፓርቲው የሚያከናውናቸውን ልዩ ልዩ ተግባሮች ለሕዝብ ያሳውቃል፣

26.5 የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴን፣ የኪነት ቡድንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ኮሚቴዎች በሰብሳቢነት ይመራል፣

26.6 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና ከፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 27፣ የውጭ ጉዳይ ኃላፊ፣

የውጭ ጉዳይ ኃላፊው ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች መካከል የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነቶችና ሥልጣን ይኖረዋል።

27.1 የፓርቲውን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ፣ ስልትና አካሄድ ያቅዳል፤ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤ ተከታታይ ጥናትም ያካሂዳል፣

27.2 በአገር ውስጥ ከሚገኙ የውጭ ኢምባሲዎች፣ ቆንስላዎች፣ ኮሚዩኒቲዎች፣ ሚሲዮኖችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር የግንኙነት ሥልት በመንደፍ ስለፓርቲው ፕሮግራምና አቋም እንዲያውቁ ያደርጋል፣

27.3 ከመሰልና አቻ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ጤናማ የትግል ግንኙት እንዲኖር በማቀድ ይሰራል፣

27.4 የውጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴንና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን ኮሚቴዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

27.5 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና ከፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 28፣ የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊ፣

የፋይናንስ ጉዳይ ኃላፊው ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አባሎች መካከል የሚመረጥ ሆኖ የሚከተሉት የሥራ ኃላፊነቶችና ሥልጣን ይኖረዋል።

28.1 የፓርቲውን የገቢ ምንጭ ያፈላልጋል፣ የገቢና የወጭ ዝርዝር የያዘ ዓመታዊ የፋይናንስ እቅድ በየበጀት ዓመቱ ያዘጋጃል፣

28.2 የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በትክክል ተጠብቆ በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅን ያጠናክራል፣

28.3 የፓርቲው ገንዘብና ንብረት በትክክል ተጠብቆ በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የሂሳብ አያያዝና የንብረት አጠባበቅን ያጠናክራል፣

28.3 የፓርቲው ሂሳብ አያያዝ በህግ ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አሠራር ሥልትን የተከተለ መሆኑን ያረጋግጣል፣

28.4 በየወቅቱ አስፈላጊ የሆኑ የሂሳብ መግለጫዎችን በማዘጋጀት እንደሁኔታው ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው፣ ለምክር ቤቱ ወይም ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፣

28.5 በየበጀት ዓመቱ የፓርቲውን ገቢና ወጭ ዝርዝር የሚያሳይ የሂሳብ መግለጫ በማዘጋጀት ለኦዲትና ኢንስፔክሽን ኮሚቴ በማቅረብ ያስመረምራል።

28.6 በሂሳብ ሥራ ላይ የተሰማሩ የፓርቲው ሠራተኞች ሥራቸውን በአግባቡ መስራታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያረጋግጣል፣

28.7 የፓርቲውን ሂሣብ በፊርማቸው ለማንቀሳቀስ ሥልጣን ከተሰጣቸው ኃላፊዎች ጋር በመሆን በጣምራ ያንቀሳቅሳል፣

28.8 የፋይናንስ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴንና ሌሎች አግባብነት ያላቸው ኮሚቴዎችን በሰብሳቢነት ይመራል፣

28.9 ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴውና ከፕሬዝዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

## አንቀጽ 29፣ የየዘርፎች ምክትል የሥራ ኃላፊዎች፣

29.1 የዋና ፀሐፊውና የሌሎች ዘርፍ ኃላፊዎች ምክትሎች ከምክር ቤቱ ቋሚ አባሎች ውስጥ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ይመረጣሉ፣

29.2 በአንቀጽ 29.1 የተገለፁት ምክትል ኃላፊዎች በማንኛውም ጊዜ የየዘርፋቸውን ዋና ኃላፊ ይረዳሉ፣ ዋና ኃላፊዎቹ በማይኖሩበት ጊዜ ተክተው ይሰራሉ።

29.3 የየዘርፉ ምክትል ኃላፊዎች ከሥራ አስኪያጅ ኮሚቴና ከየዘርፉ ኃላፊዎች የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ።

# ክፍል አራት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## አንቀጽ 30፣ የፓርቲው የገቢ ምንጭ፣

በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 52 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፊደል “ሀ” እስከ “በ” የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የፓርቲው የገቢ ምንጭ፣

30.1 ከአባሎች የሚሰበሰብ መዋጮ፣

30.2 ከደጋፊዎች የሚሰጥ እርዳታና ስጦታ፣

30.3 ለገንዘብ ማግኛ ከሚዘጋጅ ልዩ ልዩ ዝግጅት፣

30.4 መንግሥት ከሚሰጠው ድጎማ፣ ይሆናል።

30.5 ፓርቲው ፕሮግራሙን ለማስፈፀም እንዲችል ማንኛውንም ህጋዊ የሆነ የገቢ ማሰባሰቢያ እንቅስቃሴዎችንና ተግባራትን ያካሂዳል፣

## አንቀጥ 31፤ የገንዘብና ንብረት አጠቃቀም፣

31.1 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ከሚሰበስቡት ገንዘብ ላይ የተፈቀደላቸውን በጀት በሥራ ላይ አውለው ቀሪውን ለማዕከሉ ፈሰስ ያደርጋልሉ፡፡

31.2 ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ማስተላለፍ የሚገባቸውን ፈሰስ ከሦስት ወሮች በላይ ማዘግየት የለባቸውም፡፡

31.3 ማንኛውም የገንዘብና ንብረት አጠቃቀም በፓርቲው የገንዘብና የንብረት ደንብ እና በህግ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 32፤ የዲሲፕሊን እርምጃ አወሳሰድ፣

32.1 የፓርቲውን የመተዳደሪያ ደንብ የሚጥስ፣ የአባልነት ግዴታዎችን የማይፈጽምና ፓርቲውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አደጋ ላይ ሊጥሉ የሚችሉ ተግባራትን ሲፈጽም የተገኘ አባል ከኃላፊነት መነሳት እስከ አባልነት መሠረዝ የሚደርስ የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል::

32.2 በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው አካላት የፓርቲውን የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ መሠረት በማድረግ እርምጃ ወስደው ለሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ያሳውቃሉ፣ እርምጃ የተወሰደባቸው አባላትም ይግባኝ የማለት መብት አላቸው::

32.3 በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የሚቋቋመው የዲስፕሊን ኮሚቴ በራሱ አነሳሽነት ወይም ክሶች ሲቀርቡለት ጉዳዮችን የመመርመር፣ የማጣራትና ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል:: ነገር ግን ግልጽ የሆነ የፍትህ መዛባት ሁኔታ ከታየና ጉዳዩም በይግባኝ ከቀረበለት ሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ጉዳዩን ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

32.4 የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው የመጨረሻ ይግባኝ ሰሚ አካል ይሆናል፣ የፓርቲው ምክር ቤት አባላት የዲስፕሊን ጉዳይ ግን ለምክር ቤቱ ሊቀርብ ይችላል፡፡

32.5 የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ ዝርዝር መመሪያ በሥራ አስኪያጅ ኮሚቴው ወጥቶ በምክር ቤቱ ሲፀድቅ በሥራ ላይ ይውላል::

## አንቀጽ 33፤ ተፈፃሚነት የሌላቸው ተግባሮች፣

ይህንን የፓርቲ መተዳደሪያ ደንብና የፓርቲውን ዓላማ የሚፃረሩ ማናቸውም ተግባሮች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

## አንቀጽ 34፤ ፓርቲው ስለሚፈርስበት ሁኔታ፣

ፓርቲው ሊፈርስ የሚችለው፤

34.1 አባላቱ ፓርቲው እንዲፈርስ ሲጠይቁና ጠቅላላ ጉባዔው እንዲፈርስ ሲወስን፣

34.2 በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 አንቀጽ 37 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 መሰረት፣

## አንቀጽ 35፤ ደንቡን ስለማሻሻል፣

ይህ ደንብ በጠቅላላ ጉባዔው 2/3ኛ ድምጽ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ፤ 36 ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ፣

ይህ ደንብ ከጥር 24 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡